# ሁለት ምላስ

(ከያሬድ ተሾመ ኖርዌይ)

የታመመ - አስታም፣
ያዘነን - አጽናና፣

የተራብ - አጉርስ
የወደቀን - አንሳ፣

አብረኸው - ተራመድ
በሕብረት - ተነሳ

ተባብለን ነበር
ሽፍጥ ሳንጀማምር
ክፉ ቀን ሣይመጣ
ዓይን ሳናወጣ

አንዳችንም ሳንጎል
ለትግል ስንዘምር

ዋሽተን ሣንናጥቅ
የተነሣን ሳንጥል

ያልሞተን ሣንቀብር
በዘመነ አንድነት
እንዲህ ሳንኮበልል
በፌሽታው ላይ ሙሾ
በሙሾው ላይ ፌሽታ
እንዲህ ሣናምታታ
ባንድ ምላስ ሳለን
ከባብ ሳንዛመድ
የፊት እድፍ ሳንሆን
በሁለት ሳንሽረድድ።